**ፕሬስ ሪሊዝ**

**የካቲት 15 ቀን 2000 ዓ.ም**

**የኢፌዴሪ ማስታወቂያ ሚኒስቴር**

## *በሶማሊያ የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ተጠቅሞ አሁን ያለውን ሰላምና መረጋጋት ቀጣይ ለማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ተገቢ ነው*

በሶማሊያ አዲስ የተቋቋመው ካቢኔ በሽግግር መንግሥቱ ቻርተር መሰረት ኃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው አቅጣጫ እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመሩ ይታወቃል፡፡ በሞቃዲሾ ፀረ ሰላም ኃይሎች በቀቢፀ ተስፋ አልፎ አልፎ የሚቃጡትን የሰላም ማወክ ድርጊቶች በበቂ ሁኔታ ከማምከን ጎን ለጎን አዲሱ ካቢኔ ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት እያከናወናቸው ያሉ ጅማሮዎች አበረታችና ተስፋ ሰጭ እየሆነ መጥተዋል፡፡ በዚህም መሰረት በአዲስ መልክ የተዋቀረው ካቢኔ በሞቃዲሾ ከተማ ቢሮዎችን የማደራጀት ስራ፣ የመከላከያና የፖሊስ ኃይሎች ደግሞ የህብረተሰቡን ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅና ሕግና ሥርዓትን የማስከበር ተግባራትን በተሻለ ደረጃ እያካሄዱ ይገኛል፡፡

ሰላም ወዳድ ሶማሊያውያን፣ የጎሳ መሪዎችና የህብረተሰብ ተወካዮች ለሽግግር መንግሥቱ እየሰጡት ባለው ድጋፍና በመከላከያ ኃይሉ የጋራ ጥረት በሞቃዲሾና አካባቢዋ ከምንጊዜውም ይልቅ አሁን የተሻለ መረጋጋትና ሰላም ተፈጥሯል፡፡ ለዚህም ነው የአዲሱ ካቢኔ አስፈፃሚ አካላት ለቀጣይ ሥራቸው መቃናት ራሳቸውን እያደራጁና አስፈላጊ ሁኔታዎችን እያመቻቹ የሚገኙት፡፡

ዛሬ መላ የሶማሊያ ሰላም ወዳድ ሕዝቦች አገራቸው ባለፉት 16 ዓመታት ከነበረችበት እጅግ አስከፊ ሁኔታ ወጥታ ሰላማዊ ህይወት መምራት እንዲችሉ ከሽግግር መንግሥቱ ጎን ቆመው የበኩላቸውን እየተወጡ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድም የጎሳ መሪዎችና ዓባላት በሶማሊያ ዘላቂ ሰላም ሰፍኖ አገራቸውን መልሶ ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ ያላቸውን ቁርጠኝነት እያረጋገጡ ናቸው፡፡ የጎሳ መሪዎችና የህብረተሰቡ ተወካዮች ከሽግግር መንግሥቱ አስፈጻሚ አካላት ጋር በቡድንና በተናጠል እየተገናኙ በመወያየትና በመመካከር ለሶማሊያ ዘላቂ ሰላም

መስፈን መፍትሔ የሚሆኑ ሀሳቦችን እያካፈሉ ተጨባጭ ድጋፎችንም እያደረጉ ይገኛል፡፡

በሶማሊያ አሁን የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀምም መላ ሰላም ወዳድ ሶማሊያውያን በሃገራቸው አስተማማኝ ሰላም በሚፈጠርበትና ብሎም በሃገሪቱ የመልሶ ግንባታ ፕሮግራሞች ተግባራዊ በሚሆኑበት አቅጣጫ እየሰጡት ያለውን ድጋፍ ይበልጥ አጠናክረው ሊቀጥሉበት ይገባል፡፡ የሽግግር መንግሥቱም ከጎሣ መሪዎችና ተወካዮች ጋር ተቀራርቦ መስራቱን እንዲሁም በውይይትና በሰላማዊ አማራጭ ልዩነት አለን የሚሉን ወገኖችን የሶማሊያ የመልሶ ግንባታ አካል ለማድረግ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን አስፈፃሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ሊወጡ እንዲችሉ ለማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ጥረቶችንም ማጎልበት ይጠበቅበታል፡፡

ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ የሽግግሩ መንግሥት ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች እንደ እስካሁኑ ሁሉ አቅም በፈቀደ መጠን የበኩሏን ድጋፍና ትብብር ለማድረግ ዝግጁ ነች፡፡ በተመሳሳይም አህጉራዊና ሌሎች ዓለም አቀፋዊ ድርጅቶችና ተቋማት እንዲሁም ሃገራት ለሶማሊያ መልሶ ግንባታ ለተነደፉ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ተፈፃሚነት ከምንጊዜውም በበለጠ ሁኔታ ድጋፋቸውን ሊሰጡ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ በቅድሚያ በሶማሊያ ዘላቂ ሰላምን ከማረጋገጥ አኳያ የተሟላ የሰላም አስከባሪ ኃይል ለመላክና ከዚህ ጎን ለጎንም የሽግግር መንግሥቱን የአስፈፃሚ አካላት ለማደራጀትና በቀጣይም በሃገሪቱ የመልሶ ግንባታ ፕሮግራሞች ዙሪያ የሚወጡ ዕቅዶችንና አፈጻጸሞችን በገንዘብና በሎጂስቲክስ ለመደገፍ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡

አሁን በሶማሊያ የተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ይህንን ጥረት የተሳካ ለማድረግ የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ከመሆኑ አንፃር በሶማሊያ ጉዳይ መላ ሰላም ወዳድ ወገኖች በጋራና በቅንጅት መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም የአፍሪካ ህብረት፣ የተባበሩት መንግስታት፣ የአለም አቀፉ ማህበረሰብና አገራት ጥረቱን ደግፈው እንደመቆማቸው ይህንኑ ውጤታማ ለማድረግም የበኩላቸውን ድጋፍ በተግባር አጠናክረው ሊገፉበት ይገባል፡፡

# # # #